ግንባር ሃገራዊ ሓድነት ኤርትራ الجبهة الوطنية المتحدة الارترية

# Eritrean National United Front

<u>የኤርትራ ብሄራዊ ኣንድነት ግንባር</u>
ጋዜጣዊ መግለጫ
11 ሰኔ 2009

የፋሽሽቱ ኢሳያስ ኣፈወርቅ ኣስተዳደር ለሌላ ኣገር ዜጋ (ህዝቦች) የሚተርፍ ይቅርና ለራሱ ዜጎች የሚሆን ኣንዳችም መብት የማይሰጥ የወጣለት የግፍ ስርኣትና በኣለማችን ዉስጥ ካሉት ሁሉም ኣስተዳደሮች በሰብኣዊ መብት ረገጣ ቀዳማዊዉን ስፍራ የያዘ ከመሆኑም በላይ፡ በተጨማሪ በኣፍሪቃ ቀንድ ሽብርተኝነት በማራመድ መሪ ሆኖ የጥፋት እስትራተጂዉን በማካሄድ ላይ ያለ ሕገ መንግስት የሌለዉ በዲሞክራሲና ብምርጫ የማያምን፡ ራሱን እንደ ፍላስፋ፡ እንደኣዋቂ የሚቆጥር፡ ኣፍሪቃ ዉስጥ ከተፈጠሩት ኣምባገነኖች፡ ቀዳማዊዉን ቦታ የያዘ የሰዉ ምስል ያለዉ፡ ጭራቅ መሆኑ ለማንም የሰዉ ልጅ ፍጡር ያልተገለጠ ሚስጢር ሊሆን ይችላል ብለን በፍጹም ኣናምንም።

ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ ለማዉጣት ያነሳሳን ዋንኛዉ ምክንያት፡ <u>በዉጭ ኣገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፡ ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ኣለመኖሩን እያወቅን፡ ሁሉን ኣቀፍ የትግል ስልት ለማካሄድ ብቸኛዋ የስትራተጂ ቦታ ኤርትራ በመሆንዋና፡ ምርጫም ስለሌለን ከኢሳያስ ጋር መስራት የግድ ሆኖብናል በማለት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያራምዱ በማየታችን መሆኑን ግልጽ ማድረግ እንወዳለን።</u>

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፡ በኤርትራ ላይ ያሉ ህዝቦች፡ በላያቸዉ ላይ የግፍ ቀንበር ተጭኖባቸዉ፡ በጠራራ ፀሃይ እየታረዱና እየተገደሉ ባሉበት ሰዓት፡ ፋሽሽት ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ መፍትሄ ይሆናል ብላችሁ ማሰባችሁ፡ ኢሳያስን እንዳላወቃችሁትና፡ በተለይም <u>የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነዉ</u> የሚለዉን ኣስተሳሰብና እምነትን ተግባር ላይ በማዋል ተወዳዳሪ የሌለዉ ፍጡር የመሆኑን ጉዳይ በደንብ እንዳልተከታተላችሁ ተረድተናል።

<u>የኢሳያስ ጥላቻ በህ.ወ.ሓ.ት፡ ኢ.ህ.ኣ.ዲ.ግ መሪዎች ላይ ብቻ ነዉ ብሎ ማሰብና መደምደምም በጣም ኣደገኛ ነዉ።</u> ከኢሳያስ ጋር መስራት ዉጤቱና ትርፉ መዘዝ ብቻ ነዉ። በምንም ተኣምርና መለኪያ ከኢሳያስ ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን የሚጠቅም ስራ ይሰራል ብሎ ማመን ወይም ማሰብ የዋህነት ነዉ።

የፋሽሽት ኢሳያስ ኤርትራ፡ ሁሉን ኣቀፍ የትግል ስልት ለማካሄድ ብቸኛዋ የእስትራተጂ ቦታ ሆና የተመረጠችበት ምክንያት ምንድ ነዉ? ኢሳያስ ከህ.ወ.ሓ.ት ኢ.ህ.ኣ.ዲ.ግ ጋር ኣይታረቅም ከሚል ጥናት የሚነሳ ከሆነ ትክክል ነዉ። ሌላ ምክንያት ግን፡ በተለይ የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ፡ የሚታይ ኣንዳችም ነገር የለም። በኛ ኣስተያየት ነገሩ የተገላቢጦሽ ነዉ፡ ጥናቱ የፋሽሽት ኢሳያስ ኤርትራ፡ ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለማዳከም ብቸኛዋ ሁሉን ኣቀፍ የትግል ስልት የምታራምድ የጥፋት መንደር ነች ብሎ መምዘንና ማመን በተገባ ነበር እንላለን።

የፋሽሽት ኢሳያስ ምክር፡ ኣስተሳሰብና፡ የዲሞክራሲም ይሁን፡ የህግ የበላይነት ኣመለካከት፡ ኢትዮጵያን ለማፍረስ እንጂ፡ ኢትዮጵያን ለመጥቀም ያስችላል ብሎ ማሰብ በጣም ኣደገኛ ነዉ ብለን እናምናለን።

የኤርትራ ብሄራዊ ኣንድነት ግንባር፡ ለራሱ ተቃዋሚ ስለሆነ፡ ኣትቃወሙ ኣይልም፡ መቃወም ተገቢ መሆኑን ያምናል። ኣትቃወሙ ለማለትም መብት የለዉም፡ ነገር ግን በኣንድ በኩል ከፋሽሽት ኢሳያስ ጋር በመተባበርና በመተሳሰር የኤርትራን ህዝብ ሰቆቃ፡ ጭቆና፡ ግድያና ግፍ ረግጦ ማለፍና፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ጠላት የሆነዉን ኣዉሬ እንደሰዉ ቆጥሮ፡ ከርሱ ጋር ግንባር ለመስራት ሽርጉድ መካሄዱን ስለኣረጋገጥን ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ እንድናወጣ ተገደናል።

ኣሁን ያለዉ ትዉልድ፡ ከግልና ከድርጅት ጥቅም ይበልጥ፡ ኣገሩናን ህዝቡን ኣስቀድሞ ለሰከነ ትግል ማዘጋጀት ኣለበት እንጂ፡ በጊዝያዊ የፖለቲካ ዋጋ ወይም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ፡ በሚል ኣጉል ፈሊጥ፡ ከፋሽሽት ኢሳያስ ጋር ተባብሮ፡ ኢትዮጵያን ኣደጋ ላይ እስከመጣል የሚያደርስ ጭፍን ጉዞ መሻት የለበትም። የሚሻለዉ ወይም መመረጥ የሚገባዉ መንገድ፡ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት፡ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ሊያመጡ በሚችሉ ነገሮች ላይ፡ ከስሜታዊነት ዉጭ በሆነ ኣስተሳሰብ የኢትዮጵያን ዕድገትና ዲሞክራሲ፡ ግቡ ላይ ለማድረስ መጣር፡ መረባረብ ይበጃል ብለን እናምናለን።

የኢትዮጵያን ሰፊ ህዝብ የሚያሳትፍ ትግል በማካሄድ፡ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስርዓት መቀየር ይቻላል የሚል እምነት ኣለን። ሰፊዉ ህዝብ እስከፈለገዉና፡ እስከፈቀደዉ ድረስ፡ ህዝባዊ ትግል ግቡን የማይመታበት ምንም ምክንያት የለም። እኛም ከኣገራችን ዉስጥ ፋሽሽት ኢሳያስን ኣስወግደን፡ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና፡ እንዲሁም ከናንተና፡ ከሌሎች ጎረቤት ኣገሮች ጭምር፡ ተከባብረንና ተግባብተን ለመኖር ለመብቃት እየተታገልን ነን። ፋሽሽት ኢሳያስን የምንመታበትና የምናስወግድበት፡ ሁሉን ኣቀፍ ትግል ለማካሄድ ብቸኛ የእስትራተጂ ቦታ ብለን የምናየዉ መሬት እስካሁን ድረስ የለንም።

በቁርጠኝነት ለመታገልና፡ የሚጠበቀዉን መስዋእትነት ለመክፈል ፍቃዱም ዉሳኔዉም እስካለና እንዲሁም የጋራ እስትራተጂ ቀይሶ የመስራት ችግር እስካልኖረ ድረስ፡ እዉነተኛና ፍትሃዊ ትግል እንደሚያቸንፍ ስለምናዉቅ፡ ተስፋ ሳንቆርጥ ተግተን በመታገል እንገኛለን። እናንተም በቁርጠኝነት ለመታገልና፡ የሚጠበቀዉን መስዋእትነት ለመክፈል ፍቃዱም፡ ዉሳኔዉም፡ እስካላችሁ ድረስ፡ እንዲሁም በተለይ፡ የጋራ እስትራተጂ ቀይሳችሁ ያለመስራት ችግር እስካስወገዳችሁ ድረስና፡ ትግላችሁ የህዝብ ፍላጎት የሆነዉን፡ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ፡ ፋሽሽት ኢሳያስ ግፍ የሚፈጽምበት፡ ህዝቦች በጭካኔ የሚታረዱበትና የሚፈጁበት፡ እንዲሁም የኣፍሪቃ ቀንድ ኣገሮችን ለማተራመስ የሸበራ ዩኒቨርሲቲ ወዳለበት የኢሳያስ የጥፋት መንደር ጎራ ማለት ተገቢ ኣይደለም።

ኢሳያስ፡ የኢትዮጵያ ኣንድነት ተቆርቋሪ ነኝ እያለ ሲያለቅስና፡ ችግራችን ወያኔ ብቻ ነዉ በማለትም ሲያሾፍና ሲስቅም ኣይተናል፡ ኣዳምጠናል። ባጭሩ፡ በኣቶ ስለሺ ጥላሁናን (ኣርበኞች ግንባር) በኣቶ ኢሳያስ ክፍሌ (ኢትዮጵያን ሪቪዉ)፡ ከፋሽሽት ኢሳያስ ጋር የተካሄደዉን የጥያቄና መልስ ዉይይት በደንብ ተከታትለነዋል። የማያፍረዉ ኢሳያስ ግን፡ በተደጋጋሚ ግዜ ስለ ኢትዮጵያ ኣንድነት እንደሚቆረቆርና፡ ከድሮ ጀምሮ ወያኔን ስለኣንድነት የሚቻለዉን እንደመከረና፡ ኢትዮጵያን በብሄር ብሄረሰቦች መከፋፈል፡ በክልል መንግስታት ማዋቀር፡ የብሄሮችን የመገንጠል መብት ማመን፡ ትክክል ኣለመሆኑን ነግረናል፡ ወያኔ ግን ኣልሰማንም በማለት ለፍልፈዋል። ኣስመራ ዉስጥ ላሉት፡ የትግራይ ንቅናቄ፡ የቤንሻንጉል፡ የኦሮሞ፡ የጋምቤላ፡ የደቡብ፡ የኣርበኞች ግንባር፡ ንቅናቄዎች ግን ስለ ኣንድ ኢትዮጵያ መቆርቆሩን ገልጾላቸዉ ኣያዉቅም።

ኣቶ ስለሺ ጥላሁንና፡ ኣቶ ኢሳያስ ክፍሌ፡ ኢሳያስን ከኢትዮጵያዉያን ያሰባሰብናቸዉ ጥያቄዎችን ነዉ የምንጠይቅዎት በማለት ፋሽሽት ኢሳያስን ክቡር ፕረዚዳንት እያሉ በመጥራት፡ ልክ እንደኣዋቂ፡ እንደፍላስፋ ቆጥረዉ፡ ስለወያኔ፡ ስለዲሞክራሲ፡ ስለምርጫ፡ ስለሰላም፡ ስለሶማሊያ፡ ስለዳርፉር፡ስለኢጋድ፡ ስለ የኣፍሪቃ ህብረት፡ ስለ የተባበሩት መንግስታት፡ ስለኢትዮጵያ ኣንድነት እንደጠየቁትና፡ በተለይ ኣቶ ስለሺ ጥላሁን ፋሽሽት ኢሳያስ መልስ

በሚሰጥበት ሰዓት ኣድናቆቱን በመሳቅና ባማድነቅ ይጋራዉ እንደነበር በደንብ ተከታትለናል። ሆኖ ግን፡ ኢሳያስን ስልጣን መቸ እንደሚለቅና፡ ኤርትራ ዉስጥ ምርጫ መቸ እንደሚካሄድና፡ እንዲሁም የህግ የበላይነት መቸ ነዉ የሚረጋገጠዉ ብለዉ ለመጠየቅ ኣልቻሉም። ለምን እንዳልጠየቁት ለኛ ግልጽ ነዉ፡ ይቅር የዉጭ ሰዎችና፡ የራሱ ሰዎች ኣብረዉት ለረጅም ኣመታት የተታገሉ፡ ምን እንዳደረጋቸዉና የትም እንዳሉ በደንብ ጠንቅቀዉ ስለሚያዉቁ፡ ፋሽሽት ኢሳያስን የሚያዋርጥ ጥያቄ ለመጠየቅ ኣልደፈሩም።

ፋሽሽት ኢሳያስ፡ ገዳይነዉ፡ ኣዉሬነዉ፡ ጭራቅም ነዉ። ርህራሄ የሌለዉ የሰዉ ፍጡር የሚመስል ኣራዊት ነዉ። ታድያ እንዴት ነዉ ኢትዮጵያ ሰዉ እንዳጣች ወደዚህ ፋሽሽት የምትጠጋዉ፡ ከፋሽሽት ጋር በመተባበርና ግንባር በመመስረት የጦርነት ዘመቻ ላማካሄድ ሽርጉድ የምንሰማዉ፡ እንዴትነዉ ጃል ምነዉ ሌላ መንገድ ታጣ። በኛ በኩል ፋሽሽት ኢሳያስ የሁለቱም ህዝቦች ጠላት መሆኑን በደንብ ስለምናዉቅ፡ በጋራ ትግል እናጥፋዉና፡ በሁለቱ ኣገሮች መካከል እስትራተጂካዊ የሆኑ ስምምነቶችን መስርተን ተከባብረንና ተፋቅረን በሰላም እንኑር። ከፋሽሽት ኢሳያስ ጋር መስራት ማለት ግን፡ የጥፋት ሃይል፡ የሽበራ ሃይል፡ የግፍ ሃይል መሆነ ማለት መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲረዳልን በክብር እንጠይቃለን።

የኤርትራ ብሄራዊ ኣንድነት ግንባር
ዋሺንግተን ዲሲ
ሰኔ 10, 2009